# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ህዳር 29 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የተሾሙትን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተከትሎ በወያኔ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ እየተሰማ ነው ፤**

**የአህዴድ ካድሬዎች አሁንም ጥያቄያቸውን ማንሳታቸው ተጋለጠ፤**

**ከተቃዋሚ መሪዎች ጋር መደራደር ያቃተው ኃይለማርያም ደሳለኝ ከሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ለመነጋገር አስመራ ድረስ እሄዳለሁ ማለቱ አስገርሞዋል፤**

**የሻእቢያ ታጣቂዎች ድንገት ጥቃት ሰንዝረው ጉዳት መድረሳቸው ተጠቆመ፤**

የሰሞኑን የወያኔ አዲሱ ሹመት ተከትሎ ህገ መንግስቱን የሚጥስ እና ህጋዊ ያልሆነ ነው በሚል ከተለያዩ አቅጣጫዎች ከፍተኛ ተቃውሞ እየተሰነዘረበት መሆኑ ታወቀ:: ህገ መንግስቱን በይፋና በግላጭ የጣሰ በመሆኑ እንቃወማለን ሲሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራር አባላትና እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራኖች እየገለጹ መሆኑ ታውቆዋል::

እስከ ዛሬ በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እና እራሱ ወያኔ ያወጣውን ህግ በጣሰ መልኩ ሶስት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር መሾሙን ተከትሎ በሀገር ውስጥ ከፍተኛ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ መሰንበቱንም ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ካደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

በወያኔው ሕገ መንግስት በአንቀጽ 75 እና 76 ላይ አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር እና አንድ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ብቻ እንደሚያስፈልግ ስፍሮ እያለ ዛሬ በወያኔ ቡድን መሀከል በተከሰተ ሽኩቻ ብቻ ህጉን ጥሰው መሾማቸው አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን ቅሌት ጭምር ነው ሲሉም ምሁራኖቹ እየገለጹ ይገኛሉ::

ህገ መንግስቱን የመጣሰ ድርጊት ሲፈጸም የመጀመሪያው እንዳልሆነ ግልፅ ሲሆን የአሁኑ ሹመት የተደረገው አንድም የኃይለማርያም ደሳለኝ ችሎታና ብቃት የለውም ክሚል ሲሆን ሁለትም ህወሃት የሰውየውን ስልጣን ለመቆጣጠር እንዲያምቻቸው ነው የሚሉ አስተያየቶቸ እየተሰነዘሩ ነው::::

የራሳቸውን ችግር መደበቅ ልማዳቸው የነበረው እነኚሁ የወያኔ ባለስልጣናት በአሁኑ ሰዓት እየጦዘና እየከረረ ያለውን የውስጥ ክፍፍል ለመሸፈንና ለመደበቅ ሲሉ ሹመቱን በችግር ውስጥ

ለተዘፈቀው የወያኔ ድርጅቶች እንደ ጠበል ረጭተው ለማዳረስ የወሰዱት እርምጃ መሆኑን ጠቅሰው የሀገሪቱ ህግ ከሚፈቅደው ውጭ እየወሰዱት ያለው እርምጃ ግን የሁዋላ ሁዋላ ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸው ማወቅ ይገባቸዋል ሲሉም አፅንኦት ሰጥተው ይገልጻሉ፡፡

በአሁኑ ሹመት አሰጣጥ ላይ አስተያየት የሰነዘሩ የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት እንደሚሉት ከሆነ ከዚህ ቀደም ወደ ዳር ሲገፋ የነበረው ኦህዴድ ዛሬ ደግሞ ከመቼውም ግዜ በላይ ወደ ውጭ ተጥሎዋል ካሉ በሁዋላ ባለፈው ሳምንት ሹመቱ ከተሰጠ በጥቂት ቀናት ውስጥ እንደተለመደው የኦህዴዶችን አንገት ለማስደፋት ሲባል በአዳማ/ናዝሬት ድንገተኛ ስብሰባ ተጠርቶ የተደረገው የስልጣን ክፍፍል ተገቢና ትክክለኛ ነው ብላችሁ የአቋዋም መግለጫ አውጡ ተብለው እንደነበርም አጋልጠዋል፡፡

ሰሞኑን በተደረገው ሹመት ከዚህ ቀደም የህወሀት ሰዎች ከያዙት የመከላከያ... የደህንነት... ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች በተጨማሪ የዲፕሎማሲውን.....የገንዘብ ተቁዋማቱንና ሌሎች ወሳኝ ቦታዎችን በሙሉ የተቆጣጠሩ በመሆኑ ስልጣን ሁሉ ወደ ህወሀት መግባቱ ተረጋግጦዋል ሲሉ የኦህዴድ ካድሬዎች በብስጭት እና በቁጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት የሀገሪቱን ዋና ዋና ስልጣኖች የህወሀት ሰዎች ጠቅልለው የያዙበት ወቅት ሲሆን የመከላከያ ኤታማዦር ሹም ጄ/ል ሳሞራ የኑስ-ከህወሀት....ሰሞኑን በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት የተሾመው ደብጽዮን ገ/ሚካኤል የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እና ፋይናንስ ባንኮችንም......ትልቁ የሀገሪቱ ገንዘብ ሰብሳቢ ተቁዋማቶች..... የሀገር ውስጥ ገቢና ጉምሩክ.....የመሳሰሉትንና በተለይ የደህንነቱን ክፍል በሙሉ የያዘው ይሄው ግለሰብ ከህወሀት ሲሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው ሌላው ዶ/ር ቲዎድሮስ አድህኖም ዲፕሎማሲውን ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው -ከህወሀት መሆኑ የሀገሪቱ ስልጣኖች መለስ ከነበረበት ግዜ ባልተናነሰ እንዲያውም በበለጠ ሁኔታ በህወሀት እጅ ወድቋል እያሉም የሚናገሩ የፖለቲካ ተንታኞች በርካቶች ናቸው፡፡

መለስ በህይወት በነበረበት ግዜ እንኩዋን የትግራይ ተወላጆች የአሁኑን ያህል ስልጣን አልያዙም ነበር ያሉት ተንታኙ አሁን የተሰጡት ሁለት ስልጣኖች ግን እጅግ በጣም ትልቅ ሹመት መሆናቸውን ጠቅሰው ከተሾሙት አንደኛው ደብረጽዮን ገ/ሚካኤል በአሁኑ ሰዓት የህወሀት ሁለተኛ ሰው ቢሆንም ከህወሀቱ ሊቀመንበር ከአባይ ወልዱ ይልቅ ስራውን የሚሰራውና የሚቆጣጠረው እሱ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ሰሞኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው የደህንነቱና የኢኮኖሚው የበላይ ኃላፊ የሆነው የህወሀት መሪ ደብረጽዮን ገ/ሚካኤል ክንፈ ከተገደለ በሁዋላ የደህንነት ኃላፊ ሆነው ከተቀመጡት ከህወሀቶቹ  ጌታቸው አሰፋ እና ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ ጋር በመሆን የሀገሪቱን ሙሉ የደህንነት ስልጣን መቆጣጠሩንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በህወሀት ውስጥ የተፈጠረው ትርምስ አፍጥጦ በነበረበት ወቅት በሽምግልና እንዲያዝ ተደርጎ በእንጥልጥል ላይ ያለ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ህወሀትን በበላይነት እየመራ ያለው ደብረፅዮን የተባለው በረሀ አመጣሽ ግለሰብ በደህንነት እና በኢኮኖሚው ዘርፍ የአባይን ግድብ ግንባታ ሳይቀር የሚቆጣጠረው እሱና እሱ ብቻ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

መለስ በህይወት በነበረበት ወቅት ከኢትዮጵያ ህዝብ ተዘርፎ የተቋቋቋመውን ኢፈርት የተባለውን ግዙፍ የኢኮኖሚ ተቋዋም ሲያንቀሳቅሱ የነበሩት እነ አዜብ መስፍን የነበሩ ቢሆንም ከጥቂት ቀናት ወዲህ ጀምሮ ግን በዚሁ ግለሰብ ቁጥጥር ስር እየገባ መሆኑ ይነገራል::

የደህንነት ክፍሉ በምስጢር ከፍተኛ በጀት ተመድቦለት በህወሀት ሰዎች ሲንቀሳቀስ የነበረ ሲሆን የጦር ኃይሉ በበኩሉ በተመሳሳይ ግዙፍ የንግድ ተቋዋም ተቋዋቁሞለት በትርፍ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርቶ የራሱን ግዙፍ የኢኮኖሚ ጉልበት አፈርጥሞ ያለና ከ6 ቢሊዮን ብር በላይ ዓመታዊ በጀት ተመድቦለት እየተንቀሳቀሰ በህወሀቱ ጄ/ል ሳሞራ የኑስ የሚመራ ተቋዋም መሆኑን ምንጮቹ አብራርተዋል::

የህወሀት ወጣት እና ነባር ሰዎችን አንገት እያስደፋ የመጣው ይሄው ደብረጽዮን የተባለው ግለሰብ መለስ ይዞት የነበረውን የኢኮኖሚ የበላይነት ስልጣን ተረክቦ በመንግስት የተወረሱትን የኢኮኖሚ ዘርፎች እና ከፊል መንግስታዊ የሚባሉትን ኩባንያዎች ማለትም በተግባር በህወሀት ቁጥጥር ስር ያሉትን የሀገሪቱን ሁለት ሶስተኛውን ይዞታ ፍጹም በበላይነት መቆጣጠሩንም ምንጮቹ አብራርተዋል::

ለይስሙላ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ስልጣን የተሰጠው የደኢህዴኑ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከመሾሙ ጥቂት ቀናት በፊት የሀገሪቱ ህግ ከሚፈቅደው ውጭ ድንገት 34 ጄኔራሎች እንዲሾሙ የተደረገ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 25 ያህሉ የህወሀት መኮንኖች መሆናቸው የአንድ ወገን የበላይነት እንዲነግስ ለማድረግ የተቀነባበረ ዘዴ ከመሆኑም በተጨማሪ ኃይለማርያም ጨርሶ ስልጣን እንደሌለው በገሀድ ያሳየ ነበር ሲሉ መላ የሀገሪቱ ህዝብ ሲናገሩም ተደምጠው ነበር::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔ ቡድን ኢትዮጵያን ወርሮ መቶ ሺህ ኢትዮጵያውያን እንዲያልቁ ምክንያት ከሆነው ከሻእቢያ መሪዎች ጋር ለመነጋገር ፍላጎት እንዳላቸው መግለጹ አነጋጋሪ መሆኑ ታወቀ::

ስልጣኑን አሳልፎ ለህወሀቶች ሙሉ ለሙሉ ያስረከበው አዲሱ የደቡቡ ተወላጅ ኃይለማርያም ደሳለኝ ሰሞኑን ከአልጀዚራ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ እንዳለው ከሆነ አስፈላጊ ከሆነ አስመራ ድረስ ተጉዤ ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር እደራደራለሁ ሲል መግለጫ መስጠቱ የሀገር ውስጥ መነጋገሪያ ሆኖ መሰንበቱ ታውቆዋል::

በባድመ ውጊያ ወቅት ከ80 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን በጥይት አረር ሲያልቁ ለሙዋች ቤተሰቦች እንኩዋን መርዶ ሳይነገር ባለበት በአሁኑ ወቅት ከሻእቢያው መሪ ጋር ለመነጋገር እና ለመደራደር አስመራ ድረስ እሄዳለሁ ብሎ መግለጫ መስጠቱ መስዋዕት በሆኑ አትዮጵያውያን ላይ መሳለቅ ነው ሲሉ መላው በርከታ ወገኖች በንዴት እየተናገሪ ይገኛሉ::

ወያኔ ከሻዕቢያ ጋር ለመነጋገር ያለው ፍላጎት አሁን የመነጨ ሳይሆን ሙዋቹ መለስ ዜናዊ በምስጢር ጀምሮት የነበረውን ድርድር እና ይዞት የነበረውን እቅድ ለማስፈጸም እንደሆነ የተናገረው ኃይለማርያም ደሳለኝ መለስ በህይወት እያለ ከኢሳያስ ጋር ለመደራደር ከ50 ግዜ በላይ ጥያቄና ተማጽኖ አቅርቦ እንደነበረም አጋልጦዋል።

ለአፍሪካ ማጣሪያ የእግር ኳስ ጨዋታ ኢትዮጵያና ኤርትራ አንድ ምድብ ላይ በመደልደላቸው ጨዋታውን እንደማታደርግ ኤርትራ በይፋ የገለጸች ቢሆንም የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ የሰጠው... የሀገር እና የህዝቡን ክብር እና ዝና እያዳከመ የሚገኘው የወያኔ ቡድን ግን በገለልተኛ ሀገር ጨዋታው ይደረግ እያለ ተማጽኖ እያሰማ መሆኑም ታውቆዋል።

በተያያዘ ዜና የወያኔው ተላላኪ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከኢሳያስ ጋር ለመነጋገር አስመራ ድረስ እሄዳለሁ እያለ እየተማጸነ ባለበት በአሁኑ ወቅት በወያኔና በሻእቢያ መሐከል ግጭት መቀስቀሱን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋለጠ።

በጅቡቲ ድንበር ላይ በምትገኘው ጋላፊ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሻእቢያ ታጣቂዎች ድንገት በሰነዘሩት ጥቃት በሲቪል አርብቶ አደር ኢትዮጵያውያን ላይ ጉዳት ያደረሱ ከመሆኑም በላይ ግመሎቻቸውንና ከብቶቻቸውን ነድተው የወሰዱባቸው በመሆኑ ግጭቱ ሊቀሰቀስ እንደቻለ ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አጋልጦዋል።

ከጅቡቲ ድንበር 170 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ግዙፍ የወያኔ ጦር ሰፍሮ ያለ ቢሆንም የሻእቢያ ጦር ሰርጎ በመግባት በአርብቶ አደር ዜጎቻችን ላይ ጥቃት ያደረሰ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ወያኔ አጸፋዊ አርምጃ ለመውሰድ ይሁን ድንበር ለመጠበቅ ባይታወቅም ቅዳሜ ህዳር 23 ቀን 2005 ዓ.ም ግዙፍ ጦር ወደ ስፍራው መላኩን የአይን እማኞች አስረድተዋል።

ቅዳሜ እለት አንድ ብርጌድ ጦር የጫኑ ከ50 አውቶቡስ በላይ ወደ ስፍራው ሲጉዋዙ የተመለከቱ የአይን እማኞች በዚያው ዕለት ምሽት ላይ ከባድ የጦር መሳሪያ ጭምር ሲከተል እንደነበረም ጨምረው ገልፀዋል።

በሌላ ዜና የሀገር አፍራሽ እና ታሪክ በራዥ የሆነው የወያኔ ቡድን የኢትዮጵያ ታሪክ መገለጫ የሆኑትን ሐውልቶች በመንገድ ግንባታ ሰበብ እየናደ መሆኑ በመላ የሀገሪቱ ህዝብ ዘንድ ክፉኛ ብስጭትን እያስከተለ እንደሆነ ታወቀ።

በልማት ስም የሚፈጸሙ ድርጊቶች መተኪያ የሌላቸውን ቅርሶች ሊያሳጡ እንደሚችሉ እየተናገሩ የሚገኙት የሀገሪቱ ህዝቦች የወያኔ ቡድን በቅርቡ ለዘመናት የኖረውን የማንነታችን መገለጫ የሆኑትን ሐውልቶች ለማፍረስ መዘጋጀቱ ህዝብንና ሀገርን መናቅ ነው ሲሉ በቁጭት እየተናገሩ ይገኛሉ።

በአሁኑ ሰዓት እየተደረጉ ያሉት የሀገር ቅርሶች ማጠፋት ብሎም ታሪክን መናድ ወያኔ ገና ከበረሀ ሲመጡ ጀምሮ ሀገርን እና ታሪክን የማፍረስ አባዜ የተጠናወታቸው የወያኔ ቡድን ስልጣን ከያዙ ከ21 ዓመት በሁዋላም ለዘመናት ታፍሮና ተከብሮ የኖሩትን ሐውልቶች በባቡር ሀዲድ ግንባታ ስም ለመናድ ዝግጅት መጠናቀቁን ተከትሎ በህዝቡ ዘንድ ቁጣን እያስከተለም ይገኛል።

የወያኔ ቡድን አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ከገባበት ግዜ ጀምሮ የአሰብ ወደብን ለሻዕቢያ ያስረከበ .....ከጎንደር ለም መሬትን ጎምዶ ለሱዳን የሰጠ.....የሀገሪቱን ቅርሶች እና ጥቅሞች አሳልፎ እየሸጠና እየበተነ ያለ ታሪክ አጥፊ ቡድን ነው ሲሉም በቁጭት ይናገራሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የባቡር መስመር ለመዘርጋት በሚል እድሜ ጠገብ የኢትዮጵያውያን ታሪክ መገለጫ የሆኑትን የአቡነ ጴጥሮስ እና የአፄ ምኒልክ ሐውልቶችን እንደሚነካ እያወቁ በሌላ አቅጣጫ መቀየስ እና መገንባት ሲገባቸው በግዴለሽነት እና በምን ቸገረኝነት ስሜት ሊንዱት መዘጋጀታቸው አሳዛኝ እና አሳፋሪ ነው ሲል ህዝቡ እየተናገረ ይገኛል።

ሐውልቱን አንስተን መልሰን እናስቀምጣለን እያሉ የቁም ውሸት እየዋሹ የሚገኙት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ቅን ሆነው ያሰቡት ቢሆን ኖሮ ሀውልቱን ከማንሳት ይልቅ ለመንገዱ ሌላ አማራጭ መጠቀም ይገባቸው ነበር ሲሉም ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ የታሪካዊ ማንነታችን መገለጫ የሆነውን ሐውልቶች እየናዱ ትላንት በኦርቶዶክስ እምነት አማኞች ላይ መሳሪያ እየመዘዙ በየአደባባዩ ለገደሉትና ላስገደሉት የአባ ጳውሎስ ሐውልት አይፈርስም እያሉ እየሞገቱ ታሪካችንን ለመናድ መሩዋሩዋጣቸው አሳፋሪ ነው ብለዋል።

በመጨረሻም በጅማ ዩኒቨርስቲ በተቀሰቀሰ ተቃውሞ ብዙ ተማሪዎች በፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ድብደባ እንደተፈጸመባቸው ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ።

ሰኞ ህዳር 24 ቀን 2005 ዓ.ም ከረፋዱ 5 ሠዓት ላይ የጅማ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በምግብ ጥራት እና መጠን ላይ ያነሱትን ተቃውሞ ተከትሎ በዩኒቨርስቲው አስተዳደር ጥሪ የተደረገለት የፌዴራል ፖሊስ እና የኦሮሚያ ፈጥኖ ደራሽ በወሰዱት የኃይል እርምጃ ብዙ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ ከባድ ጉዳት መድረሱ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

በዕለቱ ተማሪዎቹ የሚሰጠን ዳቦ ጥራት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ መጠኑ ያነሰ በመሆኑ ይስተካከልልን ብለው ጥያቄ ቢያቀርቡም በጎ ምላሽ ከመሥጠት ይልቅ በተማሪዎቹ የቀለብ ሂሳብ ልባቸው የተደፈነው የወያኔ ካድሬ የዩኒቨርስቲው አስተዳደሮች ያለ አንዳች ማንገራገር በፌዴራል ፖሊስ እና በኦሮሚያ ልዩ ኃይል በመጠቀም እንዲደበደቡ መደረጋቸው በእጅጉ እንዳሳዘናቸው የዩኒቨርሰቲው ተማሪዎች በቁጭት ሲናገሩ መደመጡንም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

የዩኒቨርስቲው አስተዳደር እና የወያኔ ካድሬዎች የተማሪዎቹን በጀት እየቀረጠፉ ዘመናዊ መኪና ጭምር እየገዙ ሲንፈላሰሱ ተማሪዎቹ ለርሀብ በመዳረጋቸው መሰረታዊ የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ የፌዴራል ፖሊስ እና የኦሮሚያ ተወርዋሪ ፖሊሶች በጥምረት በወሰዱት እርምጃ ቁጥራቸው የበዛ ተማሪዎች ክፉኛ የተጎዱ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይ ሴት ተማሪዎች ሆዳቸውን በጀርመን ሰራሽ ዱላ በመደብደባቸው ለከፋ ህመም መዳረጋቸውን ይሄው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

ተቃውሞው ከተደረገበት ሰኞ ህዳር 24 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዓርብ ህዳር 28 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ የረባ ትምህርት እንዳልተጀመረም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።